

# የሙሴ እናት ዮካቤድ

- በሚኖሩበት ምድር ድርቁ በጣም ኃይለኛ ስለነበር ያዕቆብ፣ ልጆቹና መላ ቤተሰቡ ወደግብፅ ምድር ሄዱ። በግብፅም  እህል ማግኘት ችለው ነበር። በዚያን ጊዜ የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ በግብፅ ምድር አስተዳዳሪ ስለነበር ሌሎቹ የያዕቆብ ልጆች በግብፅ ምድር ጥሩ መስተንግዶ ተደረገላቸው። አመታት አለፉ። ያዕቆብና ልጆቹ በሙሉ ሞቱ። እንዲሁም ከእነርሱ ጋር የነበረው ትውልድም ጭምር እንዲሁ በሞት አለፈ።

- እስራኤላውያን በዚያን ጊዜ ተባዝተው ትልቅ ሕዝብ ሆነው ነበር። ፈርኦንም ከመብዛታቸው የተነሳ እነርሱን መፍራት ጀመረ። ጦርነት ቢነሳ እስራኤላውያን ከጠላቶቻቸው ወግነው ግብፃውያንን ሊዋጉ ይችላሉ። ስለዚህ የእስራኤላውያንን ልጆች ባሪያዎች አደረጋቸው። ሸክላዎችን በማበጀት፣ ከተሞችን በመገንባትና በእርሻ ውስጥ በመሰማራት በስራ እንዲጠመዱ አደረጓቸው።

- ፈርኦንም በዚያን ጊዜ በግብፅ ውስጥ አዋላጆች የነበሩትን ሲፓራና  ፉሐ ወንድ ሕፃናት ሲወለዱ እንዲገድሏቸው አዘዘ። እነኘህ ሁለት አዋላጆች ፈርኦን እንዳላቸው ሕፃናቱን ከመግደል ይልቅ ዕብራውያን እናቶችን ሲወልዱ ይረዷቸው ነበር። ሕፃናት ሲወለዱ ጉዳት ማድረስ ትክክለኛ ነገር እንዳልሆነ የተረዱ አዋላጆች ነበሩ። ስለዚህ የተለያዩ ሰበቦችን እየፈጠሩ የንጉሱን ትዕዛዝ አይፈፅሙም ነበር። ስለዚህም ንጉሱ ሕዝቡን፣ “ማንኛውም የሚወለድ ዕብራዊ ወንድ ሕፃን ወንዝ ውስጥ እንዲጣል፣ ሴት ስትወለድ ግን እንዳትገደል፣” የሚል ትዕዛዝ አወጣ።

- እስራኤላውያን በንጉሱ ትዕዛዝ እጅግ በጣም ተደናገጡ። የሚወልዷቸው ወንዶች ለጆቻቸው እንዲገደሉባቸው አይፈልጉም። ከሌዊ ወገን የሆነ እንበረም የሚባል አንድ ሰው ነበር። እርሱና ሚስቱ ዮካቤድ ሁለት ልጆች ነበሯቸው። የሴት ልጃቸው ስም ማርያም ሲሆን ወንዱ ልጃቸው ደግሞ አሮን ይባላል። ታዲያ

በዚህ አስቸጋሪ ዘመን እጅግ በጣም የሚያምር ወንድ ልጅ ወለዱ። ለሶስት ወራት ያህልም ደበቁት። የሚኖሩበት ቤትና አካባቢ ከስጋት ነፃ ስላልነበር ዮካቤድ ይህ አዲስ ልጇ በማያሰጋ ቦታ እንዲያድግላት ትፈልጋለች። በዚያን ዘመን ሰዎች ቅርጫት የሚሰሩበት ደንገል እና ቄጤማ ይሰበስቡ ነበር። ከሳር ብቻ የሚሰራ ቅርጫት ደግሞ በውሃ ላይ ሊንሳፈፍ አይችልም። ስለዚህ ዮካቤድ ዝፍትና ቅጥራን በመጠቀም ቅርጫቱ እንዲንሳፈፍ አድርጋ አዘጋጀችው። ከዚያም ሕፃኗን ቅርጫት ውስጥ አድርጋ በሸምበቆዎች መካከል በሚገኝ ወንዝ ውስጥ ለቀቀችው። ማርያምም የት እንደሚደርስና ምን እንደሚሆን ለማየት ቅርጫቱን ተከተለችው። ቅርጫቱም ከወዲህ ወዲያ እያለ የፈርኦን ልጅ ሰውነቷን ትታጠብበት ወደነበረችበት የወንዝ ዳርቻ ደረሰ። የፈርኦን ልጅ ቅርጫቱን በሸምበቆዎች መካከል ስትመለከተውም አገልጋይዋን ልካ አስመጣችው። ቅርጫቱ መከደኛ ነበረው። መከደኛው ሲከፈትም ሕፃኑ ማልቀስ ጀመረ። ልዕልቲቱም እንዲህ አለች፣ “ይህ ከዕብራውያን ሕፃናት መካከል አንደኛው ነው።” ርህሩህ ልብ ስለነበራትም ልጁ እንዲገደል በፍፁም አልፈለገችም። ልክ በዚያኑ ሰዓትም ቅርጫቱን ስትከታተለው የነበረችው ታላቅ እህቱ ማርያም ከተደበቀችበት ወጣች። ሕፃኑን የምታጠባ ሞግዚት ልታገኝላት እንደምትችልም ነገረቻት። ሞግዚቷ ማን እንደሆነች መቼም ሳትገምቱ አትቀሩም። የሕፃኑ የራሱ ወላጅ እናቱ ነበረች ሞግዚቷ! የፈርኦን ልጅም ሕፃኑን “ሙሴ” ጠራችው።

ትርጉሙም “ማውጣት” ማለት ነው። ይህንንም ያለችበት ምክንያቱ ሙሴን ከወንዝ ውስጥ ስላወጣችው ነበር።

❋ ወላጅ እናቱም ከእርሷ ተለይቶ ወደቤተ መንግስት መሄድ የሚችልበት እድሜ ላይ እስከሚደርስ በእጇ አሳደገችው። ታዲያ በዚያን ጊዜ የሙሴ ቤተሰብ ሙሴን ስለእስራኤል ታሪክ አስተምረውታል። ካደገ በኋላም ወደቤተመንግስት ወደልዕልቲቱ ተወሰደ። እርሷም እንደልጇ አድርጋ አሳደገችው። አድጎ ከቤተ መንግስት እስከሚወጣ ድረስ እንደአልጋ ወራሽ አደገ።

❋ እግዚአብሔር ዮካቤድን ተጠቅሞ ሙሴን ከሞት አዳነ። እንዲሁም እግዚአብሔር በሙሴ ሕይወት የሚፈፅመው የራሱ የሆነ ልዩ ዓላማ ነበረው። የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያድንና ከግብፅ ባርነት ነፃ አውጥቶ ወደነፃነት የሚመራቸው ሙሴ ነበር።

የዮካቤድን ታሪክ በዘፀአት ምዕራፍ ፲፣ ፪፣ እና 6 ውስጥ ማንበብ ይቻላል።

http://gardenofpraise.com